ከዚህ ሁሉ መረዳት እንደሚቻለው ከ19ኛው ክ/ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ያቆጠቆጠው ግንኙነትና አልፎም የሃይማኖትና የወታደራዊ አጋርነት ለመፍጠር የተቀሰቀሱት ሃሳቦች ሁለቱንም ወገኖች ያበረታቱና በሁለቱም ዘንድ ሩስያ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ የወደፊት እድል ልዩ የሆነ ተልእኮና ትልቅ ሚና ትጫወታለች የሚል እምነት አሳድሮ ነበር;;

በ1880ዎቹ ዓመታት ላይ የመካከለኛው ምስራቅ የፖለቲካ ሁኔታ መለዋወጥ ይጀምራል;; በ1869ዓ.ም ከስዊዝ ካናል መከፈት ጋር ይህ የዓለም ክፍል ስትራቴጂያዊ ጠቀሚነቱ እየጎላ ሲመጣ አካባቢውን በቁጥጥር ስር ለማዋል በኢምፔሪያሊስት አገሮች መሃል የነበረውም ትግል የዛኑ ያህል እየከረረ ይመጣል;; ወቅቱ የኦስማን ኢምፓየር በጦርነት ተሸንፎና ተዳክሞ እየፈራረሰ የመጣበት ሲሆን ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ግዛቶቹን እንደ ቅርጫ መቃረጥ ይጀመራል;; በ1872 እንግሊዝ ግብጽን፣ በ1878 ዓ.ም ኦስትሮ-ሀንጋሪ ቦስንያንና ጌርጸጌንያን ተወስዳለች;; በቀይ ባህር ጠረፍ የሚገኙት መሬቶችም ላይ ትግሉ ቀጥሎ እንግሊዝ ዜይላንና በርበራን፣ ጣልያን አሰብን ምፅዋንና ኢል-ቤርናንድን፣ ፈረንሳይ ደግሞ አቦኮን (ጅቡቲን) ይይዛሉ;;

ሩስያን በሚመለከት ቱርክን በማዳከምና በ1878 ወሳኝ ድል በማስገኘት ለቱርክ ኢምፓየር መውደቅ ከፍተኛውን ሚና የተጫወተች ቢሆንም ከድሉ ጋር ያገኘቸው ገድል አነስተኛ ነበር;; በጦርነቱ ደቅቃና ተዳክማ የወጣች በመሆኑ ከሌሎች የኢምፔሪያሊስት አገሮች እኩል በዚህ አለም ክፍል በቅርጫው ተካፋይ ለመሆን አቅም አልፈቀደላትም ነበር;; ሆኖም ባስገኘችው ድልና እድል ተጠቃሚ በመሆን በመካከለኛው ምስራቅ እግራቸውን በሰፊው ለመዘርጋት የቻሉት ተፏካካሪና ባላንጣዎቿ ሁኔታ አሳስቧት ነበር;; በተለይም የእንግሊዝ ግብጽን ቅኝ ማድረግ የማትቀበለው መሆኗን በተቃውሞ ገልጻለች;;

ግብጽን መቆጣጠር ማለት ስዊዝ ካናልን በእጅ ማድረግ መሆኑን የተረዳው የሩስያ መንግስት የግብጽን በእንግሊዝ እጅ መውደቅ መግታት ባይችል ወደፊት እንገሊዝ በአካባቢው የምታደርገውን መስፋፋት ማቆምና ተጽዕኖዋን መገደብ በአፍሪካ ቀንድ የሚከተለው አብይ የፖለቲካ መርህ አድርጎ ይይዛል;; በዚህ ግዜ የሩስያ የውጭ ጉዳይ መሪዎች ስለ ኢትዮጵያ የበለጠ ማስታወስ ይጀምራሉ;;

ይህንን በሚመለከት በካይሮ የሩስያ ዲፕሎማት "ልዩ ራፖር ስለ አቢሲኒያ" በሚል ርእስ በላከው ልዩ መልእክት ላይ "... በአሁኑ ግዜ በመላው አውሮፓ አገሮች ዘንድ የቅኝ ግዛት ፖለቲካ በአፍሪካ ምድር እንደ ሰደድ እሳት በተስፋፋበት ወቅት አበሲኒያ ትልቅ ትኩረትና ግምት የሚሰጣት አገር ሆናለች;; ....በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታይነታቸው ከጥንት ግዜ ጀምሮ ሩሰያን የክርስትና እምነት ጠባቂ አገር ናት ብለው ያምናሉ .... የንጉሳዊው መንግስት ግን እስካሁን ድረስ በሩቅ ከምትገኘው አቢሲኒያ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር አለመቻሉ የሚያሳዝን ነው ... ንጉስ ቴዎድሮስና ንጉስ ዮሀንስ ለመቀራረብና ግንኙነት ለማበጀት ያደረጉት ጥረት ተገቢውን ምላሽ ስላልተሰጠው ያለ ውጤት ቀርቷል;; አሁንም አቢሲኒያን በሩስያ ተፅዕኖ ስር ማስገባት ከተቻለ ያለ ብዙ ወጪና ግጭት ዋና ፖለቲካችንን ማካሄድ እንችላለን;; ይህም ጠንካራ መንደርደሪያ ሊሆነን ይችላል;;[10] ሲል ያብራራል;;

በዚህ ራፖር ላይም ኢትዮጵያ ያላትን ስትራቴጂካል አቀማመጥ ይገልፃል;; በወቅቱ ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር የሚለያያት ስፋቱ ከ100 እስከ 300 ኪ.ሜ የሚሆን ቀጭን ቀበቶ መሬት ሲሆን የክልሉም ባለቤትና ነዋሪዎች የአፋርና የሶማሌ ብሄረሰቦች ናቸው;; ይህንንም ከሰሜን ወደ ደቡብ የተዘረጋ ቀጭን የባህር መሬት ለመቆጣጠር በ80ዎቹ ዓመታት በኢትዮጵያ በእንግሊዝ በፈረንሳይና በጣሊያን መሀል ትልቅ ፍትጊያ ይካሄድ ነበር;; ኢትዮጵያ የባህር በሯን ለማስመለስ በምታደርገው ትግል አፄ ዮሀንስን መደገፍ ወደፊት ለሩስያ ሊያስገኝ የሚችለውንም ጥቅም እንዲህ ሲል ራፖሩ ይገልጻል;; " ..ግዜው ረዘመም አጠረ ምጽዋ የአብሲኒያ ወደብ መሆኗ የማይቀር ነው;; እስካሁን የባህር በር ከሌላት አቢሲኒያ ጋር የቀረበ ግንኙነት መፍጠሩ ወደፊት መርከቦቻችን ወደ ሩቅ ምስራቅ ለሚያደረጉት ጉዞ አስተማማኝ ማረፊያና ከሰል ማከማቻ ወደብ ቀይ ባህር ላይ ሊያሰገኝ ይችላል;; ..." ይላል

ሆኖም የሩስያ መንግስት በአካባቢው የሚከተለው ፀረ-እንግሊዝ ፖለቲካ ባይለወጥም ተፈላጊውን ሀይልና ቁሳቁስ አደራጅቶ ኢትዮጵያን ለመደገፍ በሁለት ምክንያቶች አልተቻለውም;; ሩስያ ከቱርክ ጋር ባደረገችው ጦርነት በድል ብትወጣም ተዳክማና ከጦርነቱም በሁዋላ ትኩረቷን ዙሪያዋ ባሉ ቅኝ ግዛቶቿ (በባልካን፣ በመካከለኛው እስያና በካውካሰስ) ላይ አድርጋ ስለነበረ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ አድርጋ በኢትዮጵያ እጇን ለማስገባት አቅም  የሚያንሳት ከመሆኑ ጋር ሌላው ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በአውሮፓ ከእንግሊዝና ከሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች የነበራትን የተወጠረ ቅራኔ በ አፍሪካ ቀንድ ላይ የጎላ የዲፕሎማቲክና አልፎም  ወታደራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ማካረርና ማባባስ አልፈለገችም ነበር;; ለዚህም ይመስላል ንጉስ ኒኮላይ አፄ ዮሀንስ ላቀረቡት የቆንስላ ግንኙነት ጥያቄ 'ግዜው አልደረሰም' ብላችሁ በቃል መልሱለት ብለው ያዘዙት;;

በአፄ ዮሀንስ እግር የተተኩት አፄ ምንሊክ በ1889 ዓ.ም ማሽኮቭ በተባለ ሩስያዊ አማካይነት ለንጉስ አሌክሳንደር ሳልሳዊ በሁለቱ አገሮች መሀከል የጠበቀ ግንኙነት ይፈጠር ዘንድ ያላቸውን ፍላጎትና ምኞት የሚገልጽና እርዳታ የሚጠይቅ ደብዳቤ አስይዘው ይልካሉ;; በ1891 ዓ.ም ይኸው ሰው የሩስያ የመልከአ-ምድር ሳይንስ ጥናት ማህበር አባል ተብሎና የሳይንሳዊ ምርምር ኤክስፒዲሽን በሚል ሽፋን የመንግስት ኦፊሲያል መልእክተኛ በመሆን የመልስ ደብዳቤ ይዞ ይመለሳል;; ሆኖም የመልስ ደብዳቤው ይዘት የሁለቱ አገሮች መቀራረብ የሩስያ ፍላጎት መሆኑን በደፈናው የሚገልጽ ነገር ግን መቼና ምን አይነት መልክ ሊኖረው እንደሚችል የቀረጠ መልስ ያልያዘ በጥቅሉና በጥንቃቄ የተዘጋጀ ነበር;; እርዳታውንም በሚመለከት አፄ ምንሊክን ምን አይነት እርዳታ እንደሚሹ መልሶ የሚጠይቅ ነበር;;

የሩስያ ባልስልጣናት ይህን የመልከአ-ምድር ጥናት ኤክስፒዲሺን የመንግስት ተልዕኮ ያለው መሆኑን ለመደበቅ የሞከሩ ቢሆንም ከጣልያንና ከእንግሊዝ ሊሰወር አልቻለም;; በአውሮፓ በወቅቱ ፀረ እንግሊዝ የሆነ የሩስያና የፈረንሳይ ህብረት ተፈጥሮ ስለነበረ መልእክተኛውን ማሽኮቭን ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ያደረገውን ጉዞ ፈረንሳይ አጃቢ ሰጥታ መሸኘቷም አጋሯ ሩስያን በአፍሪካ እግሯን እንድታሰገባ ያደረገችው ድጋፍ መሆኑና የሩስያም በኢትዮጵያ መቆናጠጥ ቀስ በቀስ ፈረንሳይ በግብፅ ያጣችውን ተፅዕኖ ለማስመለስ የታለመ እቅድ ነው የሚል ግምት አሰጥቶ ነበር;; ለንደን ታይምስ በጥር ወር እትሙ ላይ ' ይህ ኤክሰፒዲሽን እኛ በ1868 ካደረግነው (አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ለመሰዋት ያበቃቸውን
 የናፒየርን እክስፒዲሽን ማለቱ ነው) የበለጠ ሰፊና ውጤቱ ለረዥም ግዜ የሚቆይ ለውጥ የሚያመጣ ግብና ዓላማ ያለው ነው ብሎ አትቶ ነበር;;' [11]

ሆኖም የሩስያ መንግስት ዓላማ በዚህ ኤክስፒዲሽን አማካይነት ከኢትዮጵያ ጋር የሚፈጠረው ግንኙነት በምን መልኩና እስከምን ደረጃ ድረስ ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት በአጥኝ ቡድን መልክ የተላከ እንጂ ከዚህ በላይ ዓላማና ተልዕኮ አልነበረውም;;

አፄ ምንሊክ በላኩት ሁለተኛ ደብዳቤ ላይ ጣልያኖች ከራስ መንገሻ ጋር አብረው ተንኮልና ደባ እየፈጸሙባቸው መሆኑን የሚገልፅና የውጫሌን ውልም ይዘቱን በመቀየር የአገራቸውን ልዕልና እየተፈታተኑ መሆናቸውን በማስረዳት የሩስያን ድጋፍ እንደሚሹ የሚያብራራ ሲሆን ለጦር ምኒሰትሩም በላኩት ደብዳቤ የኢትዮጵያን ጦር በአውሮፓ መልክ ሊያደራጁላቸውና ሊያሰለጥኑላቸው የሚችሉ የጦር አማካሪዎች እንዲልኩላቸው የሚጠይቅ መልእክት የያዘ ነበር;; [12]

ይሁን እንጂ የአፄ ምንሊክ ጥረትም ሆነ በሩስያ ውስጥ የኢትዮጵያና የሩስያ ወዳጅነት እንዲጠናከር የሚሹ አፍቃሬ-ኢትዮጵያ ሩስያውያን ግፊት እንዲሁም የሩስያ የሃይማኖት መሪዎች ጉትጎታ ቁጥብና ልዝብ የነበረውን የሩስያ መንግስት ኦፊሲአል አቋም ሊለውጠው አልቻለም;;

በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን የጣሊያን ቅኝ የሚያደርገውን የውጫሌን ውል ሩሰያ ባትቀበለውም እንግሊዝና ጀርመን የተቀበሉት በመሆኑ በዚህ ሁኔታ ግንኙነት መፍጠርም ሆነ የጦር እርዳታ ማቀበል ጸበኛ ባላጋራን  መነካካትይሆናል በሚል እምነት ሁኔታው እስኪጠራ የሩስያ ባለስልጣናት ገለልተኛ መሆኑን የመረጡ ሲሆን በዚህም ምክንያት ኦፊሲያል ፖለቲካው መሃል ላይ የቀረ መጣሁ-ቀረሁ አቋም ሊይዝ በቅቷል;;

የአድዋ ጦርነት ዋዜማ ላይ ኢትዮጵያ ደርሶ ይመለስ ከነበረው የሩስያ መልክአ-ምድር ጥናት ማህበር ቡድን ጋር ሚያዚያ 1895 ዓ.ም አራት አባላትን የያዘ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መልእክተኛ ቡድን በፈታውራሪ ዳምጤ መሪነት ወደ ሩስያ ይሄዳል;; የቡድኑም ተልዕኮ የንጉስ አሌክሳንደር ሳልሳዊን እረፍት ምክንያት በማድረግ የሀዘን መግለጫ ለማድረስና የአልጋ ወራሹን ንግስና ለመመረቅ ሲሆን ከዚህም ጋር ኢትዮጵያ ፊቷ ከተደቀነው ከጣልያን ጋር የማይቀር ጦርነት የጦር መሳሪያ እርዳታና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ለማግኘትም አብሮ የታቀደ ነበር;;

ሆኖም የጦር ምኒስትሩ ለአፄ ምንሊክ በስጦታ መልክ ከላከው 135 ዘመናዊ ጠብመንጃ በስተቀር የኢትዮጵያን መከላከያ የሚያጠናክር ወታደራዊ እርዳታ ለማግኘት የመንግስት አቋም ሳይፈቅድ ቀርቷል;; በሌላ በኩል ግን ራሱ የመልእክተኛው ቡድን በሩስያ መገኘቱ ብቻ በውጫሌ ውል መሰረት ኢትዮጵያን ለማግለል ይደረግ የነበረውን የኢምፔሪያለስት አገሮችን ፖሊሲና አድማ በማፍረስ ከፍተኛ የዲፕሎማሲና የሞራል ድጋፍ ሆኗል;;

የመልእክተኛው ቡድን በተመለሰ በሰባት ወሩ መጋቢት 1 1986 ኢትዮጵያ በጣልያን ላይ አንፀባራቂውን አፍሪካዊ ድል - የአድዋን ድል- ተጎናጽፋ ነፃነቷንና ልዕልናዋን ለመላው ዓለም ታረጋግጣለች;; በሩስያ የአድዋ ድልም ከፍተኛ አድናቆትንና ደስታን የፈጠረ ሲሆን የሩስያንና የኢትዮጵያን ግንኙነትም ከስሩ በመለወጥ አዲስ ምእራፍ ይከፍታል;; በሩስያ ፕሬስና በአፍቃሬ-ኢትዮጵያ ሩስያውያን ዘንድም ታላቅ ስሜት ቀስቅሶ የቀይ መሰቀል የህክምና እርዳታ ለማሰባሰብና ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ሰፊ ዘመቻና ዝግጅት ይደረጋል;; በውጤቱም ግንቦት 21 1896 ዓ.ም በከፍተኛ ወጭ በርካታ የህክምና መገልገያዎችና 41 የህክምና ባለሙያዎችን የያዘ የህክምና ብርጌድ ወደ ኢትዮጵያ ይላካል;;

ይህም የህክምና ቡድን ለ70 ቀናት አዲስ አበባ በቆየበት ወቅት ከ5000 በላይ ለሚሆኑ የአድዋ ጦርነት ቁስለኞች የህክምና አገልግሎት የሰጠ ሲሆን መሰረታዊ የህክምና እርዳታ ምክሮችንና እውቀቶችን በአማርኛ አስተርጉሞ አሰራጭቷል;; የሩስያ ቀይ መስቀል በሩስያ መንግስት ድጋፍ ያደረገው ይህ ልባዊና ወንድማዊ እርዳታ በሁለቱ አገሮች መሀከል ያለውን ግንኙነት ጥልቀትና ሰብአዊነት እንዲኖረው ያደረገ ሲሆን የህክምና ቡድኑ ከሁለት ወር በላይ አገልግሎት ሰጥቶ ወደ አገሩ ሲመለስም አንድ የህክምና ዶክተርና ሁለት ረዳቶች በቋሚነት ቀርተው ዛሬ ባልቻ ሆስፒታል በመባል የሚታወቀውን ቆርቋሪ ለመሆን በቅተዋል;;

በዘሁ ግዜም አቶ ዮሴፍ የተባሉ የአፄ ምንሊክ ልዩ መልእክተኛ ኢትዮጵያ ወደብ ስለምታገኝበት ሁኔታ ከሩስያ ባለስልጣናት ጋር ለመነጋገር ሩስያ ደርሰው ተመልሰው ነበር;;

የአድዋ ድል ኢትዮጵያ በማንም ቅኝ ወይም የሞግዚት ጥላ ስር ያልሆነችና ልዕልናዋ የተጠበቀ አገር መሆኗን በማረጋገጡ ጠንቃቃና ልዝብ የነበረውን የሩስያ ፖለቲካ በሙሉ ልብ እንዲንቀሳቀስና ቀጥተኛ ርምጃ እንዲወስድ በር ከፍቷል;; በመላው አውሮፓ ኢትዮጵያ ያገኘችው ታዋቂነትና ተደማጭነት፣ የኢትዮጵያ መልእክተኞች በሩስያ ተገኝተው የፈጸሙት ተልዕኮና የቀይ መስቀሉ በኢትዮጵያ አገልግሎት መጀመሩ እነኚህ የግንኙነት መቋጠሪያ ገመዶች መነሻና መንደርደሪያ ሆነው የሩስያ መሪዎች ከኢትዮጵያ ጋር የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለመመስረት ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋል;; በዚህም ለረዥም ግዜ የታለመው የሁለቱ አገሮች ቋሚ ግንኙነት እውን ሆኖ አንድ ርከን ይራመዳል;;

በ20ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ የካቲት 5 1898 ዓ.ም የመጀመሪያው የሩስያ የዲፕሎማቲክ አባላትን የያዘው ልኡክ አዲስ አበባ ሲገባም ታላቅ የክብር አቀባበል ተደርጎለት የሁለቱ አገሮች ግንኙነት በዚህ መልኩ ሊመሰረት በቅቷል;;

ሩስያ ኢትዮጵያን በሚመለከት የምትከተለው ፖሊሲም ለመጀመሪያው የሩስያ ዲፕሎማት በተሰጠው የስራ መመሪያ ላይ እንዲህ ተገለጾ ነበር;; " ... እኛ በኢትዮጵያ ላይ የምንሻው ምንም አይነት የጥቅም ፍላጎት አይኖረንም;; ንጉስ ምንሊክ ስልጣኑንና መንግስቱን ለማጠናከር ሰላምና እድገት ለማምጣት የሚያደርገውን ጥረት እንደግፋለን;; ዋናው ቀጥተኛ ተልዕኮችሁ ከንጉሱ ጋር ቅርበትን በመፍጠር የመተማመንና የመረዳዳት መንፈስን እንድታጠናክሩና የእኛ ጠላቶች ከሆኑት የውጭ ሀይላት ተንኮልና ሸር እንድትጠብቁት ነው;; በተለይም መርዘኛና የዘረፋ ፖሊሲ

ከምትከተለው ከእንግሊዝ እንድትከላከሉት ነው;; ...." ይላል;; በሌላ አነጋገር የሩስያ የውጭ ጉዳይ መምሪያ ተወካዩ አድርጎ ኢትዮጵያ ለማስቀምጥ የፈለገው አምባሳደር ለአፄ ምንሊክ በፖለቲካ አማካሪነት እንዲያገለግልም ጭምር ነው ማለት ይቻላል;; በዚህም የኢትዮጵያን ነጻነትና ልዕልና መደገፍ የሩስያ በአፍሪካ ፀረ እንግሊዝ ፖለቲካ አንዱ አካል ነበር;;

ይቀጥላል